# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 300 ጥር 30 2006 ገጽ 1

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግንቦት7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለባዕዳን መሬታችንን፣ አገራችንን፣ ነፃነታችንን ሰጥተን ከሚገኘው ጥቅም ... ባለቅኔው እንዳለው ... ሰውነታችን ታውቆ፣ ክብራችን ተጠብቆ ሳርም ይሁን መቅመቆ መብላት እንመርጣለን። የመሬት ቅርምት በአስቸኳይ ይገታ። አገራችንን ለማዳን ቆርጠን እንነሳ።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ግንቦት 7 በአለም ዙሪያ ከሚገኙ አባላቱ ጋር መከረ

ግንቦት 7 የፍትህ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት በተዘጋጀ የድርጅቱ የስራ እቅድ ላይ በዓለም ዙሪያ ከሚገኙ ዓባላቶቹ ጋር አመርቂ ውይይት አካሄደ። ባለፈው ቅዳሜና እሁድ የተደረጉትን እነዚህን አሳታፊ ውይይቶች የንቅናቄው ከፍተኛ አመራሮች እንደመሯቸውም ተያይዞ ተጠቅሷል።

በሁሉም ቦታ ፍጹም አሳታፊ የነበረውንና ሰአታትን የወሰደውን ይህን ውይይት የመሩት እነኝህ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራሮች ከድርጅቱ ምስረታ እስካሁን ድረስ ያለውን የድርጅቱን ጉዞ ባጭሩ ማብራራታቸውን የጠቀሰው ዘጋቢያችን ለቀጣይ ሁለት አመታት ምን መደረግ አለበት የሚለውን የስራ እቅድ ለተሳታፊዎች በማቅረብ ከፍተኛ ውይይት ከተደረገበት በኋላ በሁሉም ቦታ በአባላት ሙሉ ድምጽ ተቀባይነት አግኝቶ መጽደቁን ዘጋቢያችን ጨምሮ ገልጿል።

( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## የቀድሞዊ የጋምቤላ ክልል አስተዳዳሪ አገር ጥሎ ኮበለለ

ከሀገር ከወጣ ሚስጥር ያወጣል በሚል ስጋት በስም ስልጣን የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ዲኤታ ተብሎ ወደ ወያኔ የተንኮል ሸክርክሪት ተስቦ የነበረውና በጉጅሌው ወያኔ ከፍተኛ ክትትልና ጥበቃ ይደረግበት የነበረው የጋምቤላ ክልል የቀድሞ ፕሬዚዳንት ኦሞት አባንግ ከሀገር መኮብለሉ ተሰማ። በተለይም በጋምቤላ ክልል ለተፈፀመው የአኝዋኮች የጅምላ ጭፍጨፋና በሺዎች መሰደድ፤ ከሟቹ መለስ ዜናዊ ቀጥሎ በግንባር ቀደምነት ተጠያቂ የነበረው ይህ ግለሰብ፤ በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ምስክር ሆኖ ይቀርብና ሚስጥራችን ይጋለጣል በሚል ፍራቻ፤ በፋሽስት ወያኔ መንደር ከፍተኛ ድንጋጤ በመፈጠሩ ግለሰቡን ለመያዝ ጥንቃቄ የተሞላበት ከፍተኛ ዘመቻ መጀመሩ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች ታውቋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ እጆቹ በንጹሃን ደም የተቸማለቀውንና የቀድሞውን የጋምቤላ ክልል ፕሬዚዳንት ኦሞት አባንግን በዘር ማጽዳት ወንጀል ዓለማቀፉ ወንጀል ፍርድ ቤት ፊት ለማቅረብ ብዛት ያላቸው ዓለማቀፍ ተቋማት በከፍተኛ ሁኔታ እየሰሩ መሆናቸው የታወቀ ሲሆን ለዚህም አስፈላጊና በቂ መረጃዎች እንደተሰበሰቡ እኚሁ ውስት አዋቂ ምንጮች አክለው ጠቁመዋል።

( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ከሳዑዲ የተመለሱ ኢትዮጵያውያን የምንበላዉ አጣን ሲሉ አማረሩ

በአረመኔው ጉጅሌ ወያኔ አገዛዝ ምክንያት በሳውዲም በሃገራችንም በደል እየተፈፀመብን፡ የግፍን ጽዋን እየተጐነጨን እንገኛለን ያሉት እነዚሁ ተመላሾች ጥፋታችን ምን እንደሆነ ባናውቅም የድረሱልን ጥሪ እንኳ ለወገን እንዳናደርስ ታፍነናል፡ ማስፈራሪያና ዛቻ ድብደባም ጭምር እየደረሰብን ነው ሲሉ በምሬት ያሉበትን ሁኔታ ለዘጋቢያችን አስረድተዋል። በተደጋጋሚም የተቃውሞ ሰልፍ ለመውጧት ጥረት ቢያደርጉም በወያኔ ቅጥረኛ አረመኔ ፖሊሶች መደብደባቸውን ገልፀዋል። በርካታ ተመላሾች ንብረታቸውን እስካሁን እንዳልተረከቡ በመግለፅ የሚመለከተውን አካል በተደጋጋሚ ብንጠይቅም አጥጋቢ ምላሽ አላገኘንም፡ ሱዳን ተራግፏል ከዛ አልመጣም መባላቸውን እለቅሶ በተቀላቀለበት ምሬት ለዘጋቢያችን አስረድተዋል። እኒሁ በርካታ ተመላሾች በእጃችሁ ምንም ነገር እንዳት ይዞ ስለተባልን ገንዘባችንንም ጨርቃችንንም ሻንጣ ውስጥ ነበር ያስቀመጥነው ያሉ ሲሆን፡ የከፋ ችግር ውስጥ መሆናችን እየታወቀ ከውሃ ውጪ ወያኔ ያደረገልን እርዳታ ምንም የለም፡ በረሃብ ከማለቃችን በፊት ድረሱን ሲሉ ድምፃቸውን አሰምተዋል። በዚህ የፋሽስት አገዛዝ ቸልተኝነት ምክንያት በሳውዲ አረቢያ በርካታ ወገኖቻችን በአደባባይ መገደላችውን፡ ሴት እህቶቻችን መደፈራችውን በአለም ፊት እንድናፍርና አገታችንን እንድንደፋ ያደረገን አሰቃቂ በደል ሲፈፀምብን በዝምታ ለማለፍ መሞከራቸው የሚታወስ ነው። ሆኖም በውጭና ሃገር ውስጥ ያሉ ኢትዮጵያውያኖች በጋራ ሆ ብለው በመነሳት የተቀናጀ ርብርብ በማድረግ በርካቶቹን ለሃገራቸው እንዲበቁ መደረጋቸው የሚታወስ ሲሆን ሃፍረተቢሱ የወያኔ ቡድን በተቃራኒው ስደተኞችን የፖለቲካ አጀንዳ መጠቀሚያ ለማድረግ ወደ ሃገራቸው መልሻለሁ በማለት ሲደሰኩሩ እንደነበርም የሚታወስ ነው።

## አገር ዉስጥና በውጭ አገሮች የሚኖሩ የአማራ ተወላጆች ከፍተኛ ተቃዉሞ በማሳማት ላይ ናቸዉ

በወያኔ አገዛዝ ስር የአማራ ክልል ምክትል ፕሬዚዳንት እና የወያኔ ጭራ የሆነው የብአዴን ጽህፈት ቤት ሃላፊ የሆነው አለምነው መኮንን “የአማራው ህዝብ ሰንፋጭ የሆነ ትምክተኝነት የተጠናወተው በመሆኑ በቤንሻንጉልና በሌሎችም ቦታዎች ለመሰደዱ ምክንያት ሆኖታል” በማለት በአማራ ህዝብ ላይ መሳለቁን የሰማነው ባሳለፍነው ሳምንት ነው። አለምነው መኮነን ከዚህም በተጨማሪ አማራው “በባዶ እግሩ እየሄደ የሚናገረው ንግግር ግን መርዝ ነው” በማለት እመራዋለሁ በሚለው ህዝብ ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ተሳልቋል። የዚህን የወያኔ ባለስልጣን በአማራ ህዝብ ላይ መሳለቅ ተከትሎም በርካታ ኢትዮጵያዊያን ቁጣቸውን እየገለጹ ነው። በተለይ በተለያዩ ማህበራዊ መገናኛ መንገዶች በርካታ ኢትዮጵያዊያን የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት ስርዓት አልባነት እና ዋልጌነት መረኑን እየለቀቀ መምጣቱን እና የማን አለብኝነት ስሜታቸው ጫፍ መድርሱን በስፋት ገልጸዋል። የአማራው ህዝብ ዝምታ እና ጭቆናን አሜን ብሎ መቀበሉም ለዚህ አይነት ውርደት እንዳበቃው የገለጹ አሉ።

የወያኔው ሎሌ አያሌው መኮነን እመራዋለው የሚለውን የአማራው ህዝብ ለመፃፍ በሚከብዱ ፀያፍ ቃላት ሲሳደቡ የሚያስደምጥ የድምጽ ማስረጃ ከተለቀቀ በኋላ በክልሉ ከፍተኛ ቁጣ መቀስቀሱን በክልሉ የፋሽስቱ ወያኔ ተቀጽላ በሆነው የብአዴን ካድሬዎች ውስጥም ከፍተኛ ሽኩቻና አለመግባባት መፈጠሩንና ዝግ ስብሰባ ላይ መሆናቸውን ለድርጅታችን ቅርበት ያላቸው ምንጮቻችን አጋልጠዋል። አለምነው መኮነን በፋሽስቱ ወያኔ የተጋተውን የአማራ ጥላቻ ካድሬዎቹን

( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## አሰቃቂ ረሀብ በደቡብ እና ምስራቅ ኢትዮጵያ መከሰቱ ተሰማ

ኢሳትን ዋቢ አድርጐ ዘጋቢያችን እንዳደረሰን በደቡብ እና ምስራቅ ኢትዮጵያ አስከፊ ረሀብ መከሰቱን ተከትሎ የህዝቡ ህልውና አደጋ ውስጥ መውደቁን ገልጿል። ችግሩም በአለማቀፍ የመገናኛ ብዙሀንና የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን በስፋት የመነጋገርያ አርዕስት መሆኑን የታወቀ ሲሆን የሲኤን ቢሲ ዘጋቢ እንደገለጸው ችግሩን ለመቅረፍ እስከ 100 ሚሊዮን የእንግሊዝ ፓውንድ ያስፈልጋል ሲልም ግምቱን አስቀምጧል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የያዘው የምግብ ክምችት ማለቁንም በዘገባው የተገለፀ ሲሆን፡ እንደ ሲኤን ቢሲ ዘገባ በአፍሪካ ወደ 14 ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ አስቸኳይ የምግብ እርዳታ የሚፈልግ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ወደ 10 ሚሊዮን የሚጠጋው ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን ይፋ አድርጓል። የጉጅሌው ወያኔ አሽከር ተፈራ ደርበው ከሰሞኑን በፓርላማ ተገኝተው የተለመደ የቅጥፈት ሪፖርቱን ያቀረበ ሲሆን በሪፖርቱም ከ2 ሚሊዮን በላይ ዜጎች አፋጣኝ የምግብ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል ሲል ለተሰበሰቡት አሻንጉሊት የፖርላማው አባላት መግለፁ የሚታወስ ነው፣ ሆኖም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ባወጣው ሪፖርት ግን አፋጣኝ ምግብ የሚፈልጉ ሰዎችን ቁጥር ወደ 10 ሚሊዮን ይደርሳል ሲል ትንበያውን አስታውቋል። ፋሽስቱ ወያኔ በዘረጋው አድሎዋዊ አገዛዝ ምክንያት አብዛኛው ህዝብ በጠኔ እየተመታ፡ ጥቂት ለስርአቱ ቅርበት ያላቸው ካድሬዎች ብቻ የተደላደለ ኑሮ የሚኖሩባትን ኢትዬጵያ እንደፈጠሩ ይታወቃል።

## የወያኔ ደህንነት አባላት ናይሮቢ ድረስ ዘልቀዉ ኢትዮጵያዉያንን አፍነዉ ወሰዱ

የወያኔ የደህንነት ሃይሎች ከኬንያ አራት ኢትዮጵያዊያንን አፍነው ወደ ኢትዮጵያ መመለሳቸውን የምስራቅ አፍሪካ ሰብዓዊ መብቶች ሊግ በዚህ ባሳለፍነው ሳምንት አስታውቋል። አራቱ ኢትዮጵያዊያን በቅድሚያ የተያዙት በኬንያ የጸረ-ሽብር ግብረ ሃይል ሲሆን ግብረሃይሉ ለወያኔ የደህንነት ሃይሎች አሳልፎ ሰጥቷቸዋል። የምስራቅ አፍሪካ ሰብአዊ መብቶች ሊግ እንዳስታወቀው ቱምሳ ሮባ ካቲሶ፣ ጫላ አብደላ፣ ናሚ አብደላ እና ስሙ በውል ያልታወቀው አራተኛ ሰው ናቸው ከኬንያ ተላልፈው ለወያኔ የተሰጡት። የወያኔ ደህንነቶች በቅርቡ 2 የኦጋዴን መሪዎችን ኬንያ ውስጥ አፍነው መውሰዳቸውም ይታወቃል። ሰሞኑን በወያኔ ወህኒ ቤት በግፍ ግርፋት እና ስቃይ ተፈጽሞበት ወህኒ ቤት የሞተውን የሰብዓዊ መብት ታጋይ ተስፋየ ጨመዳ ጨምሮ ሌሎች የኦሮሞ ነጻነት ግንባር አባላትም እንዲሁ ከኬንያ ታፍነው መወሰዳቸው የሚታወስ ነው።

## የመሬት ቅርምት በአስቸኳይ ይገታ!!!

“የግብርና ሚኒስትር” በሚል “የሆድ ሲያውቅ፤ ዶሮ ማታ” ስያሜ የወያኔ የመሬት ሽያጭ ጉዳይ አስፈፃሚው የሆነው የሥርዓቱ ቀንደኛ አገልጋይ “መሬት መቀራመት ኢትዮጵያን ጭራሽ አይመለከታትም” ብሎ ሲናገር የሰማነው እና ያነበብነው በከፍተኛ ትዝብት ነው።

ለመሆኑ የመሬት ቅርምት ከኢትዮጵያ በላይ ማንን ሊመለከት ነው? ሱዳንን፣ ኤርትራን፣ ሳውዲን፣ ቻይናን፣ ህንድን ወይስ አሜሪካን? ከራሱ ከወያኔ ሹማምንት የተራረፈው መሬት ለአረብ አገራትና ለእስያ ቱጃሮች በነፃ የሚታደለው ኢትዮጵያ ውስጥ አይደለምን? ባዕዳን የሚረከቡት መሬት ስፋት በሄክታር መለካት ሲሰለቻቸው “ቤልጂየምን የሚያክል” እያሉ በስጦታ ያገኙትን መሬት በአገር ስፋት የሚለኩት ኢትዮጵያ ውስጥ አይደለምን? የመሬት ቅርምት ኢትዮጵያን ካልተመለከተ ከቶ ማንን ሊመለከት ነው?

ወያኔ ለም መሬት ለራሱ ማግበስበሱ ሳያንስ “ልማታዊ ባለሀብቶች” እያለ ለሚያሞካሻቸው ለቅርብም ለሩቅም አገራት ቱጃሮች ሰጥቶ ባለሀገሩን አርሶ አደር ሜዳ ላይ በተነ። መጤው ቱጃር ባለመሬት ሆኖ ባለሀገሩ ለስደት አሊያም ለቀን ሠራተኝነት ተዳረገ። ይህ ግፍ የሚፈጥረው ስቃይ የማይበቃ ይመስል “በእቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” እንዲሉ መሬት ሻጩ “የመንግሥትና የሕዝብ ሀብት የሆኑ ነፃ መሬቶችን ብቻ ነው ለሰፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንት የምንሰጠው። ማንም ከቀዬው አልተፈናቀለም” እያለ ይዘባበትብናል። “የመንግሥትና የሕዝብ ሀብት” የሚባለው መሬት የወያኔ የግል ሀብት ከሆነ ሃያ ሶስት ዓመታት መቆጠራቸው እኛ ብቻ ሳንሆን እሱም ያውቀዋል።

አባቶቻችንና እናቶቻችን ለብናኝ አፈር በመሰሰት ጎብኚዎችን እግር አሳጥበው ሲሸኙ እንዳልነበር ዛሬ በልማት ስም ከጋምቤላ እስከ መተማ፣ ከባሌ እስከ ሰላሌ፣ ከከፋ እስከ አፋር ያለው መሬታችን በሙሉ ወይ በወያኔ ሹማምንት አሊያም በባዕዳን ቱዳሮች ይዞታ ሥር ሆኗል። ኢትዮጵያዊያን አርሶ አደሮች፣ ወንዶችና ሴቶች፣ ጎልማሳዎችና ወጣቶች፣ ሕፃናት ሳይቀር የአዳዲሶቹ ባለመሬቶች ተቀጣሪዎች ሆነዋል። ጉልተኛው ሥርዓት ከቀድሞው በባሰ መልኩ ተመልሶ መጥቷል።

ወያኔ እንደሚያወራው ሰፋፊ መሬቶችን የመስጠት ዓላማው ግብርናችንን ለማዘመን ከሆነ ኢትዮጵያዊያን ባለሀብቶች ጠፍተው ነው እሩቅ ምስራቅ እስያ ድረስ የተጓዘው? እነሱስ ለምንድነው ለሊዝ የሚጠየቁትን እዚህ ግባ የማይባለውን ገንዘብ እንኳን ከራሷ ከኢትዮጵያ ተበድረው የሚከፍሉት? ይህ ምን ዓይነት ሥርዓት ነው? ከዛሬ አርባና አምሳ አመታት በፊት በሁመራ፣ ተንዳሆና ስምጥ ሸለቆዎች ውስጥ ሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎች የነበሯቸው ኢትዮጵያዊያን ነበሩ። ያኔ ኖረው ዛሬ እንደምን ላይኖሩ ቻሉ? የመሬት ባለቤት የመሆን መብት ያለው ኢትዮጵያዊ ወያኔ ብቻ እንዲሆን የተደረገው ለምንድነው? ኢትዮጵያ፣ ወያኔ ወይም የወያኔ አሽከር ላልሆነ ኢትዮጵያዊ ምኑ ነች? ባለሃገሩን መሬት አልባ፤ ባዕዳንን ደግሞ ባለመሬት ማድረግ ምን ያስከትላል?

ኢትዮጵያ ውስጥ መሬት እጅግ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ግብዓት መሆኑ ከማንም የተሰወረ አይደለም። ኢትዮጵያ ውስጥ መሬት ከግብዓትም በላይ የፓለቲካ ሥልጣን ምንጭም ነው። ለዚህም ነው በኢትዮጵያ ፓለቲካ የመሬት ጥያቄ ቁልፍ የፓለቲካ ጥያቄ ሆኖ የቆየው። ደርግ መሬትን ከጉልተኞችም ከአርሶ አደሮችም በአዋጅ ቀምቶ የመንግሥት በማድረግ መንግሥትን አሳብጦ ገበሬውን አዳከመው። ወያኔ ይኸንኑ መሬት ያለአዋጅ ከመንግሥት ቀምቶ የራሱ በማድረግ ራሱን አሳብጦ ገበሬውን ከቀደሞው በባሰ አዳከመው። አሁን ደግሞ ይባስ ብሎ ይህንኑ መሬት ለባዕዳን በመስጠት ገበሬውን በአጠቃላይ ከመሬት ነጥሎ የቀን ሠራተኛ እያደረገው ነው። ይህ ከጪሰኝነት እጅግ የባሰ ባርነት ነው።

በወያኔ እና ታማኝ ተላላኪዎቹ እየተፈፀመ ያለው የመሬት ቅርምት ኢትዮጵያዊያንን አገር የሚያሳጣ፤ ስብዕናችንን የሚያዋርድ፤ ክብራችንን የሚገፍ፤ ሀብታችንን የሚያዘርፍ በመሆኑ በአስቸኳይ መቆም ይኖርበታል።

ሰው ባገሩ ሰው በወንዙ
ቢበላ ሳር ቢበላ መቅመቆ
ይታወቅ የለም ወይ ሰውነቱ ታውቆ

ግንቦት7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለባዕዳን መሬታችንን፣ አገራችንን፣ ነፃነታችንን ሰጥተን ከሚገኘው ጥቅም ... ባለቅኔው እንዳለው ... ሰውነታችን ታውቆ፣ ክብራችን ተጠብቆ ሳርም ይሁን መቅመቆ መብላት እንመርጣለን። የመሬት ቅርምት በአስቸኳይ ይገታ። አገራችንን ለማዳን ቆርጠን እንነሳ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## የወያኔ ደህንነት አባላት ናይሮቢ ድረስ ዘልቀዉ ኢትዮጵያዉያንን አፍነዉ ወሰዱ

የወያኔ የደህንነት ሃይሎች ከኬንያ አራት ኢትዮጵያዊያንን አፍነው ወደ ኢትዮጵያ መመለሳቸውን የምስራቅ አፍሪካ ሰብዓዊ መብቶች ሊግ በዚህ ባሳለፍነው ሳምንት አስታውቋል። አራቱ ኢትዮጵያዊያን በቅድሚያ የተያዙት በኬንያ የጸረ-ሽብር ግብረ ሃይል ሲሆን ግብረሃይሉ ለወያኔ የደህንነት ሃይሎች አሳልፎ ሰጥቷቸዋል። የምስራቅ አፍሪካ ሰብአዊ መብቶች ሊግ እንዳስታወቀው ቱምሳ ሮባ ካቲሶ፣ ጫላ አብደላ፣ ናሚ አብደላ እና ስሙ በውል ያልታወቀው አራተኛ ሰው ናቸው ከኬንያ ተላልፈው ለወያኔ የተሰጡት። የወያኔ ደህንነቶች በቅርቡ 2 የኦጋዴን መሪዎችን ኬንያ ውስጥ አፍነው መውሰዳቸውም ይታወቃል። ሰሞኑን በወያኔ ወህኒ ቤት በግፍ ግርፋት እና ስቃይ ተፈጽሞበት ወህኒ ቤት የሞተውን የሰብዓዊ መብት ታጋይ ተስፋየ ጨመዳ ጨምሮ ሌሎች የኦሮሞ ነጻነት ግንባር አባላትም እንዲሁ ከኬንያ ታፍነው መወሰዳቸው የሚታወስ ነው።

## ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የአንደድነቱን አስራት ጣሴን አሰረ

የወያኔ አገዛዝ ህዝብ ለማወናበድ እና ለማታለል አኬልዳማ በሚል ርዕስ የሰራውን መያዣ መጨበጫ የሌለው የቴሌቪዥን ፕሮግራም በመተቸታቸው ምክንያት ብቻ የአንድነት ፓርቲ አመራር አቶ አስራት ጣሴ መታሰራቸው በዚህ ባሳለፍነው ሳምንት ነው የተነገረው። አቶ አስራት ጣሴ አዲስ ጉዳይ በተባለው መጽሄት ትችታቸውን ስለጻፉ ብቻ አትንኩኝ ባዩ ወያኔ ለእስር ዳርጓቸዋል። አቶ አስራት በወያኔው ካንጋሮ ፍርድ ቤት ባለፈው አርብ ጥር 30 ቀን 2006 ዓመተ ምህረት ክስ ተምስርቶባቸው የቀረቡ ቢሆንም ፍርድቤቱ ጉዳዩ እስኪጣራ ታስረው እንዲቆዩ ወስኗል። ወያኔ በተደጋጋሚ አከብረዋለሁ በሚለው በራሱ ህገመንግስት እንኳን ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ቢደነግግም አቶ አስራትን የመሳሰሉ ሃሳባቸውን በነጻነት ስለገለጹ ብቻ ወህኒ የተወረወሩ በርካታ ኢትዮጵያዊያን እንዳሉ የሚታወቅ ነው።

## የሳዑዲ ተመላሾች አሁንም የአገር ያለህ እንዳሉ ነዉ

ባሳለፍነው ሳምንት ጥር 27 ቀን 2006 ዓመተ ምህረት ከሳውዲ አረብያ የተመለሱ ኢትዮጵያዊያን የወያኔ አገዛዝ በስማችን እየነገደብን ነው በማለት አዲስ አበባ ውስጥ ሰልፍ መውጣታቸው በተመለከተ የመነጋገሪያ ጉዳይ ሆኖ ሰንብቷል። ከሳውድ አረብያ ተመሳሾቹ ልጆቻቸውን ይዘው ልብሶቻቸውን በፌስታል አንጠልጥለው መሄጃ አጥተናል በማለት እና በወያኔ አገዛዝ አትኩሮት ተነፍገናል በማለት በአደባባይ ሰልፍ ወጥተው ብሶታቸውን አሰምተዋል።በሰልፉ ንብረታቸው እንዳልደረሳቸው፣ አትኩሮት አልተሰጣቸው እና እርዳታው የት እንደገባ ግራ እንደተጋቡ እንዲሁም ከውሃ ውጪ አገዛዙ ያደረገላቸው እገዛ እንደሌለ አሳውቀዋል። የወያኔ አገዛዝ በበኩሉ ከሳውዲ አረብያ የተመለሱ ኢትዮጵያዊያንን ማቋቋሚያ በሚል ከሃገር ውስጥም ከውጭ ሃገርም ገንዘብ ያሰባሰበ እና በማሰባሰብ ላይ የሚገኝ ቢሆንም የሰበሰበውን ገንዘብ የት እንዳሰገባው የሚታወቅ ነገር የለም።

## ግንቦት 7 በአለም ዙሪያ ከሚገኙ አባላቱ ጋር

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በስብሰባው ወቅት ለፍትህ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ የሚደረገው ጉዞ ከታሰበው እቅድ በላይ በፍጥነት እየተጓዘ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን ይህም በአባላቱ ከፍተኛ ቁርጠኝነት የተገኘ መሆኑ በየውይይቱ በአጽንኦት ተገልጿል። እኛ ከተባበርን የምንፈልገውን ከማድረግ የሚያግደን ሃይል የለም፣ የወገኖቻችን ስቃይ የሚያበቃበት የድሉ ምዕራፍ ላይም እንገኛለን ስለሆነም ሁላችንም በከፍተኛ የትግል መንፈስ ለመጨረሻው የድል ጉዞ በከፍተኛ ወኔ እንነሳ በሚል የትግል ጥሪም ተላልፏል።

በየከተሞች ከነበሩ የውይይቱ ተሳታፊዎች ለተነሱ በርካታ ጥያቄዎች አጥጋቢ ምላሽ የተሰጠ ሲሆን አባላቱ በአዲስ የስራ መንፈስና ወኔ ለእቅዱ ስኬት እንደሚሰሩ መናገራቸውን የጠቆመው ዘጋቢአችን በአካል በስልክና በመሳሰሉት የመገናኛ መንገዶች ያነጋገራቸው በተለያዩ ከተሞች ውይይቱን የተሳተፉ አንዳንድ የድርጅቱ አባላት በተለይም በቀረበው የሁለት አመቱ የስራ እቅድ ደስተኞች በመሆናቸው ለስኬቱም ከምን ግዜውም በላይ እንደሚሰሩና ትግሉ ለሚጠይቀው ሁሉ መስዋእትነትን ለመክፈል ራሳቸውን ማዘጋጀታቸውን ዘጋቢያችን ጨምሮ ገልጿል።

# የመሬት ቅርምቱ እንደገና ሲቃኝ

እቺን ዛሬ ይገፔላችሁ የቀረብኩትን መጣጥፌን ለመጻፍ ጣቶቼንና የኮምፒተሩን መክተቢያ ሳገናኝ አንድ በኢቲቪ እየተላለፈ የሚገኝ ጉደኛ የእንግሊዝኛ ፕሮግራም ተመለከትኩና መጻፌን አቋርጬ ያንን የማልወደዉን የወያኔ ቲሌቪዥን መመልከት ጀመርኩ። ወጣቷ ሴት ጋዜጠኛ ለፈረንጆችና አዲስ አበባን ለማያውቋት ቄንጠኛ የኢትዮጵያዉያን ስለዚህች የስቃይ ከተማ ቆንጆ ምስል ለመሳል ስትቃትት አየኋት። ጋዜጠኛዋ በጥቂት የዳንስ ቤት መብራቶችና በጥቂት ዘመነኛ ዳንኪራ ረጋጮች፣ በጥቂት ተምነሽናሾችና በጥቂት ገንዘብ መንዛሪዎች የሚሊዮኖች እሥር ቤት የሆነችውን አዲስ አበባን የአፍሪካ የልማት መዲና እንደሆነች ለመናገር ባይሳካላትም ብዙ ሞከረች። የአዲስ አበባን እዉነት እኛ የወያኔን ፍርፋሪ ንቀን "ምንም ቢሆን ኢትዮጵያዊነት" ብለን ለአገራችንና ለሂሊናችን ያደርን ዜጎች እናዉቀዋለን። ስድስት ሚሊዮን ህዝብ በሚኖርባት አዲሰ አበባ ዉስጥ ጥቂቶች ቢቀማጠሉባትና የሰማይን ጣሪያ በኋላ እግሯ ረግጣ እንዳራቀችው በቅሎ አለልክ ጠግበው ሌት ተቀን እየፈነጠዙ ያሻቸውን ቢያደርጉ አዲስ አበባና አዲስ አበቤዎች አልፎላቸዋል ማለት እንዳልሆነ ኢቲቪዎችም ሆኑ ወያኔዎች ሊሸፋፍኑት እንደማይችሉ ልናስታውሳቸው ይገባል።

ብዙ የአፍሪካ በተለይም የኢትዮጵያ መንግሥታት ኩረጃ ይወዳሉ። ይህንን የሚያደርጉት ከራሳቸው ማመንጨት የማይችሉ ቀፎ ራሶች ስለሆኑ ሊሆን ይችላል። በቂ የመንግሥት አመራር ዕውቀትና ችሎታ ስለሌላቸውም ሊሆን ይችላል፤ ወይም ችሎታና ዕውቀት ያላቸውን የአገራችንን ምሁራን ስለማያስጠጉና ከደደቡ ጭንቅላታቸው አሟጠው ሊያወጡት የሚችሉት የሕዝብ አስተዳደር ጥበብ ስለሌላቸው ሊሆንም ይችላል። ዋናው ጉዳይ ግን ከሕዝባቸው ሥነ ልቦናዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ሕይወት ጋር ፍጹም ሊስማሙ የማይችሉ ኩረጃዎችን ከሌሎች ሀገራት በተለይም አደጉ ከሚባሉና በስንትና ስንት ተሞክሮ ከተፈተኑ መንግሥታት እንዳለ እየገለበጡ በሀገርና በሕዝብ መቀለድን እንደዋና መዝናኛቸው ያደረጉት ይመስላሉ፤ አለማወቃቸውን ሊያውቁም ፈቃደኞች አይደሉም። ሶሻሊዝም ቅጅ ነው፤ የሠፈራ ፕሮግራም ቅጅ ነው፤ ሕገ መንግሥት ቅጅ ነው፤ የአስተዳደር መዋቅሩ ቅጅ ነው፤ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች አወቃቀር ቅጅ ነው፤ ከሞላ ጎደል ሁሉም ነገር ግልብጥ ወይም ቅጂ ነው። ያልተገለበጠ ነገር የለም። እኛም ተገልብጠናል፤ ኢትዮጵያዊነታችን ቀርቶ ሌላ ሌላ ነገር ሆነናል ወይም እየሆንን ነው። ግልብጥነት ከዚህ በላይ የለም። ብዙዎቹ ነገሮች ሲኮረጁ ግን ስማቸውና ቅርጻቸው እንጂ ከአንጀት ለሀገር ዕድገትና ልማት ታስቦ አይደለም። በዚህ ላይ የአገዛዙ ባለስልጣኖች ውሸት አይጣል ነዉ፤ ወያኔዎች ለውሸትና ስለውሸት የቆረቡ ናቸው። ከእነሱ አንደበት እውነት እንደናፈቀን ይሄዉና ሩብ ምዕተ አመት ሊሞላን ነዉ። መንግሥት በተለዋወጠ ቁጥር የሚተኩት መሪዎችና ጭፍሮቻቸው በውሸት የተጠመቁ ናቸው - የመሪዎቻችን ዉሸት ደግሞ ሲቸግረዉ እንደሚዋሸዉ እንደ ተራዉ ዜጋ ዉሸት ተራ ዉሸት አይደለም፤ የመሪዎቻችን ዉሸት እንደ ሰዉ በእግሩ ቆሞ የሚሄድ ትልቅ ዉሸት ነዉ። ለምሳሌ -አንዲትም ትንኝ አልገደልኩም፤አንድም አማራ ከሚኖርበት አካባቢ አልተፈናቀለም፤ አንድም ኢትዮጵያዊ በዐረቡ ዓለም አልተንገላታም፤ አንድም ኢትዮጵያዊ በፖለቲካ ምክንያት አልታሠረም፤ አንድም ዜጋ በተቃውሞ ሠልፉ ምክንያት አልተገደለም ወይም ማረሚያ ቤት አልገባም፤ ለዉጭ ባለኃብቶች መሬት ለመስጠት ሲባል አንድም ዜጋ ከመኖሪያ ቦታው አልተፈናቀለም ወዘተ።

የወያኔን ቅጥ ያጣ ዉሸት አንድ ምሽት ቀርቶ አመት ሙሉ ባወራዉም ተናግሬ አልጨርሰዉምና ዛሬ የማወራችሁ ስለ ወያኔ ዉሸት አይደለም። ዛሬ የማወራችሁ መሬት ቅርምት ስለሚባለው የወያኔ አንዱ ከዉጭ የተኮረጀ ፋሽን ነዉ። በመሠረቱ ቀደም ሲል እንዳልኩት ወያኔ በተፈጥሮው ዐይንና ጆሮ ስለሌለው እንጂ በዚህ ጉዳይም ያልተባለ የለም። መሬታችንን በርካሽ የገዙትን የህንድ ባለኃብቶችን ጨምሮ ፈረንጁም ሀበሻውም ብዙ ተናግሮበታል፤ ብዙም ጽፎበታል። ሆኖም ሁኔታው እየተባባሰ ከመሄድ በስተቀር የተለወጠ ምንም ነገር የለም። የዛሬዉ ጩኸቴም ወያኔ ሰምቶን ይለወጣል ከሚል ቅዠት አይደለም። ይልቁንም ዛሬ የአገራችን ለምለም መሬት ለባዕዳን በርካሽ ከተሸበሸበ ከአመታት በኋላ "የመሬት ቅርምት" እያልኩ የምወተዉተዉ እንደ እኔ የወያኔን ለመደምሰስ በህይወቱ ቆርጦ ኢትዮጵያዊነት ወይም ሞት የሚል ቆራጥ ሰዉ ባገኝ ብዬ ነዉ።

ሰሞኑን የወያኔዉ የግብርና ሚኒስቴር፣ "የውጭ ባለሀብቶች በግብርና ኢንቬስትመንት ላይ ለመሰማራት ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን ወስደው ለማልማት እንጂ፣ መሬት ለመቀራመት ብለው ወደ ኢትዮጵያ አልገቡም" ብሎ ሲናገር ተደምጧል። ኢትዮጵያ ዉስጥ የአብዛኛው ገበሬ የእርሻ መሬት ይዞታ እጅግ በጣም አነስተኛ ነዉ፤ ይህ አነስተኛ ይዞታ ደግሞ እንኳን ለሽያጭ ሊቀርብ ገበሬዉንና ቤተሰቡን ማስተዳደርም አይችልም። ታዲያ የእነዚህ ደሃ ገበሬዎች መሬት ሳይነካ ከዬት የመጣ መሬት ነዉ ለውጪዎቹ ባለሀብቶች "ሰፋፊ እርሻ" እያተባለ የሚሰጣቸው? እነሱስ መሬቱን በየትኛዉም መንገድ ያግኙት - ለመሆኑ ይህ ክስተት "የመሬት ቅርምት" ካልተባለ ሌላ ምን ሊባል ይችላል?

በነገራችን ላይ የመሬት ቅርምቱ የኢትዮጵያን ደሃ ገበሬ የእርሻና የመኖሪያ ቦታ በመቀማት ብቻ የተወሰነ አይደለም፤ ወይም የመሬት ቅርምቱ በገጠር የእርሻ መሬቶች አካባቢ ብቻ የተወሰነ ክስተት አይደለም። በየከተማዉ በተለይም በአዲስ አበባና አካባቢዋ እጅግ በጣም የሚዘገንን የመሬት ዘረፋ እየተካሄደ ነው። የወያኔ ዘረኞች በልማት ስም ለከተማዉ ነዋሪ ተገቢውን ካሣ ሳይከፍሉ መሬቱን እንዲለቅ ያስገድዱታል፤ አለዚያም የገበያ ዋጋዉ ከሚሊዮኖች የሚቆጠር ብር የሚያወጣን የግል ይዞታ የወያኔ ፍርደ ገምድል መሃንዲሶች መቶና ሁለት መቶ ሺህ ብር ብቻ ይገምቱና ባለንብረቱን ባዶ እጁን ያስቀሩታል። አንድ ታታሪ ዜጋ ዕድሜ ልኩን የኖረበትን ቦታ አንድ ወያኔ ከበላዮቹ የተጻፈ ደብዳቤ ይዞ መጥቶ ያፈናቅለዋል። ይህ ሁሉ የሚያሳየን ኢትዮጵያ ውስጥ ንብረት አለኝ ማለት የማይቻልበት ደረጃ ላይ እንደተደረሰ ነዉ።

ሌላዉ የሚያሳዝነዉ ነገር በሰፋፊ እርሻዎች ስም የገጠሩን መሬት የሚቀራመቱት በአብዛኛዉ የዉጭ ባለኃብቶች ሲሆኑ አዲስ አበባ ዉስጥ ከደሃዉ ኢትዮጵያዊ ከተሜና ገበሬ እየተቀማ የሚቸበቸበዉን መሬት የሚቀራመቱት ደግሞ በአብዛኛዉ ለገዛ ወገኖቻቸዉ ምንም ደንታ የሌላቸዉ ኢትዮጵያዉያን ናቸዉ። በተለይ በወያኔ የሚረገጠዉን የኢትዮጵያ ገበሬና ሰራተኛ ታግለዉ ነጻ ማዉጣት ሲገባቸዉ ጭራሽ ህመሙን የሚያባብሱበት በነፃነት በዉጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን ናቸዉ።

አገራችን ኢትዮጵያ የራሳቸዉን ደሃ ገበሬዎች ከይዞታቸዉ እያፈናቀሉ ለምለም የእርሻ መሬታቸዉን ለባዕዳን ቱጃሮች ከሚሸጡ የአለማችን ደሃ አገሮች ዉስጥ ግንባር ቀደሚ ናት። ኢትዮጵያን ጨምሮ ብዙ የኢስያ፤ የላቲን አሜሪካና የአፍሪካ አገሮች ልማት፤ የካፒታል ከምችትና ተክኖሎጂ ሽግግርን እንደ ምክንያት እየደረደሩ ለምለም የእርሻ መሬታቸዉን ለባዕዳን ነጋዴዎች መሸጥ ከጀመሩ ብዙ አመታት አስቆጥረዋል። ይህንን "የመሬት ቅርምት" በሚል ስያሜ የሚታወቀዉን ክስተት ከመነሻዉ ጀምሮ በሰፊዉ የተከታተሉና ያጠኑ እንደ ኦክላንድ ኢንስቲትዩት አይነት የጥናትና ምርምር ተቋሞች ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚካሄደዉን የመሬት ቅርምት በሌሎች ኋላ ቀር አገሮች ዉስጥ ከሚታየዉ የመሬት ቅርምት ለየት አድርገዉ እንደሚመለከቱት በተደጋጋሚ ባወጡት የጥናት ዉጤታቸዉ ይፋ አድርገዋል። በመሰረቱ መሬታቸዉን ለባዕዳን የሚሸጡ አገሮች ሁሉም የራሳቸዉን ዜጎች ከመሬታቸዉ ላይ የሚያፈናቅሉ ቢሆንም ኢትዮጵያ ዉስጥ ግን አንደኛ ተፈናቃዮች ካሳ አይከፈላቸዉም፤ ሁለተኛ ከመሬት ሽያጩ አገሪቱ ተጠቃሚ አይደለችም፤ ሦስተኛ ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች የኢትዮጵያን ለምለም መሬት ለባዕዳን የሚቸበችቡት ዋጋ በዬትኛዉም የአለም ክፍል ታይቶም ተሰምቶም የማይታወቅ ርካሽ ዋጋ ነዉ።

የዛሬ አራት አመት የሳዑዲ አረቢያ፤ የህንድና የቻይና ባለኃብቶች ቤልጂምን የሚያክል ሰፊና ለምለም የእርሻ መሬት ጋምቤላ፤ኦሮሚያና ቤንሻንጉል ዉስጥ ሲቀራመቱ በወቅቱ የወያኔ ባለስልጣኖች የሰጡት ምክንያት የዉጭ ባለኃብቶች ገበሬዉን ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ ጋር ያስተዋዉቁታል፤ የዉጭ ምንዛሬ ምንጭ ይሆናሉ ወይም ኢትዮጵያ ዉስጥ ስር የሰደደዉን የስራ አጥነት ችግር ያቃልላሉ የሚል ነበር። ይህንን ዉኃ የማያቋጥር ምክንያት በወቅቱ ግንቦት ሰባትን ጨምሮ ሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶች፤ አያሌ የዉጭና የአገር ዉስጥ ተመራማሪዎችና እንዲሁም ከመሬታቸዉ የተፈናቀሉ ገበሬዎች አጥብቀዉ ተቃዉመዉት ነበር። ሆኖም በመሬት ቅርምቱ ዋና ተጠቃሚዎች የሆኑትና ከኛ ዉጭ አዋቂ የለም ባዮቹ እብሪተኛ የወያኔ መሪዎች ማንንም አንሰማም ብለዉ በመሬት ቅርምቱ ገፉበት።

ዛሬ ከአራት አመት በኋላ በተግባር እንደታየዉ የአገራችን ለምለም መሬት በርካሽ የተቸበቸበላቸዉ የዉጭ ባለኃብቶች ይሆናሉ ወይም ያደርጋሉ የተባሉትን ነገር ምኑንም ሳይሆኑና ሳያደርጉ ከተረከቡት መሬት ዉስጥ አብዛኛዉን ተቃፍዉ ቁጭ እንዳሉ ሲሆን፤ ከመሬታቸዉ የተፈናቀሉት የአገራችን ደሃ ገበሬዎች ደግሞ በየጎረቤት አገሩ የስደት ኑሮዉን እየገፉት ነዉ። እዚህ ላይ አንድ በጣም የገረመን ነገር ቢኖር አነዚህ የአገሪቱን የዉጭ ምንዛሪ ችግር ያቃልላሉ የተባለላቸዉ የዉጭ ባለኃብቶች ጭራሽ ከአገር ዉስጥ ባንኮች የተበደሩትን ገንዝብ መመለስ አቅቷቸዉ ከአበዳሪ ባንኮች ጋር እሰጥ አገባ ዉስጥ ተዘፍቀዉ መታየታቸዉ ነዉ።

በቅርቡ የግብርና ሚኒስትሩ ተፈራ ደርበዉ "ሰፋፊ የእርሻ ኢንቨስትመንቶች እንደታሰቡት ዉጤታማ አልሆኑም" ብሎ የወያኔን የመሬት ቅርምት ፖሊሲ ዉጤት አልባነት ለፓርላማዉ ሲናገር ተድምጧል፤ ሆኖም ለአገራቸዉና ለህዝባቸዉ ከልብ የሚቆረቆሩ አንድ የፓርላማዉ አባል በኢትዮጵያ መሬትና በኢትዮጵያ ገንዘብ ለምንድነዉ የዉጭ ኩባንያዎች መጥተዉ የሚያለሙት ብለዉ ለጠየቁት ጥያቄ ግን አግባብ ያለዉ መልስ መስጠት ሳይችል ቀርቷል።

የኢትዮጵያ ገበሬ መጨቆንና መራብ የትግላቸው መነሻ እንደሆነ የነገሩንና "መሬት የሚሸጠውና የሚለወጠው በኢሕአዴግ ከርሰ መቃብር ላይ ነው" እያሉ ቡራ ከረዩ ሲሉ የከረሙት የወያኔ ዘረኞች ዛሬ ያንን ታገልንለት የሚሉትን ገበሬ ከመሬቱ አፈናቅለዉ መሬቱን ለባዕዳን ከሸጡ በኋላ አይናቸዉን በጨዉ ታጥበዉ የውጭ ባለሀብቶች የመሬት ቅርምት ኢትዮጵያን አይመለከትም" ደግሞም የመሬት ቅርምቱ አንድም ሰዉ ከመሬቱ አላፈናቀለም እያሉ ነጭ ዉሸት መዋሸት ጀምረዋል።

( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ወያኔ የሃይማኖት ተቋማበትን የሚመለከት አዋጅ ሊያዉጅ በዝግጅት ላይ መሆኑ ተሰማ

ሁሉንም ነገር ካልተቆጣጠርኩ ባዩ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ እሱ እራሱ ያበላሸዉን የአገራችንን በሐይማኖች ጉዳዮች ተቻችሎ የመኖር ባህል ለማሻሻል አዋጅ አርቅቆ ለማዉጣት ዝግጅቱን እያጠናቀቀ መሆኑን ከወደ አዲስ አበባ የደረስ ዜና ያስረዳል። በመጀመሪያ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን ህግና ስርዐት ዉጭ የራሱን ካድሬ ጳጳስ አድርጎ ጥንታዊቷን ቤ/ክርስቲያን የተቆጣጠረዉ ወያኔ በለመደ እጁ የሙስሊሙን ህብረተሰብም ለመቆጣጠር እንዲያመቸዉ የራሱን መጂሊስ መሾሙ የሚታወስ ነዉ። በእነዚህ ሁለት ግዙፍ የአገሪቱ የሐይማኖት ተቋማት የዉስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብቶ አገሪቱን ሲያናጋ የከረመዉ ወያኔ አሁን ደግሞ መንግስታዊ ህገ ወጥነትና ስርዐት አልባነት በአዋጅ የሚወገድ ይመስል አዋጅ ለማወጅ ጉድ ጉዱን ተያይዞታል።

ወያኔ ይህንኑ በረቂቅ ደረጃ ያለዉን አዋጅ በተለመከተ ከተለያዩ የህብረተሰብ ኣባላት ጋር አመክርበታለሁ በሚል ትልቅ ሴሚናር አዋሳ ዉስጥ ማሰጋጀቱን የደቡብ ኢትዮጵያ ዘጋቢዎቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ። የሴሚናሩን መጀመር አስመልክቶ በስልክ ያናገርናቸዉ ዘጋቢዎቻችን እንደነገሩን ከሆነ ይህ በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የተዘጋጀውና የሃይማኖት እሴቶችን ሊያጎለብት ይችላል የተባለለት ረቂቅ አዋጅ ጥር 30 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ ለሶስት ቀናት አዋሳ ከተማ ዉስጥ ይመለከታቸዋል ተብሎ ለተሰባሰቡ ሰዎች ቀርቦ ዉይይት እንደሚካሄድበት ለመወቅ ተችሏል። በዚሁ ስብሰባ ላይ በዋንኛነት የሚሳተፉት በአገሪቱ አሉ የሚባሉት 945 ያህል የእምነት ተቋማት መሆናቸውም ታውቆአል። መንግስት የሙስሊም ማህበረሰብ የሙብት ጥያቄ ማንሳታቸውን ተከትሎ ለውይይት በተደጋጋሚ ሲያገኛቸው የነበሩትን የመፍትሄ አፈላላጊ ኮምቴ አባላት በአክራሪነትና በሽብርተኘነት ወንጅሎ እስር ቤት ከከተተ ወዲህ “መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው፣አንዱ በሌላው ስራ ጣልቃ አይገባም” የሚለውን ሕገመንግስታዊ ድንጋጌ በመዘንጋት በሃይማኖት ጉዳይ እጁን ሙሉ በሙሉ ማስገባቱን ታዛቢዎች ይገልጻሉ።

መንግስት ረቂቅ ህጉ በሃይማኖት ስም ይደረጋሉ የሚላቸውን የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችን ለመግታት ይስችለኛል ብሎ ያምናል። የሃማኖት ተቁዋማቱ በስብሰባው ላይ እንዲገኙ ከመጋበዝ ባለፈ የረቂቅ አዋጁ ኮፒ አስቀድሞ እንዲደርሳቸው እንዳልተደረገ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ምንጮቻችን ጠቁመዋል። የሃይማኖት ተቋማት የሕግ ሰውነትን በተመለከተ ለመጀመሪያ ጊዜ በሕግ የተደነገገው በ1952 ዓ.ም በወጣው የፍትሐ ብሔር ሕግ ነው። የፍትሐ ብሔር ሕጉ በወቅቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን አቋቁሞ፣ ሌሎች የሃይማኖት ተቋማት ሕጉን ተከትሎ በሚወጣ ልዩ ደንብ እንደሚመዘገቡ መደንገጉ ይታወቃል። በደርግ ዘመንም ሃይማኖትን የተመለከተ ድንጋጌ ወጥቶ አያውቅም።

ኢህአዴግ መራሹ መንግስት ያወጣው ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 27 ላይ ማንኛውም ሰው የማሰብ፣የህሊናና የሃይማኖት ነጻነት እንዳለው በግልጽ ደነግጋል።ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም መቀበል ፣ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣የመተግበር የማስተማር ወይም የመግለጽ መብትን ያካትታል። ከዚህ በተጨማሪም የሃማኖት ተከታዮች ሃማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችላቸውን የሃማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማት ማቋቋም እንደሚችሉና ወላጆች ህጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸው መሰረት የሃይማኖታዊና የመልካም ስነምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸው የማሳደግ መብት እንዳላቸው ደንግጓል

## የቀድሞዊ የጋምቤላ ክልል አስተዳዳሪ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ዓለም ወደ አንዲት ትንሽ መንደርነት በተቀየረችበት አሁን ያለንበት የቴክኖሎጂ ዘመን እንኳን ሕዝብ ለመደበቅ ፈቃደኛ ሳይሆን ይቅርና ቢሆንኳ ይህን ያህል አሰቃቂ ወንጀል ሰርቶ በምንም መንገድ ማምለጥ አይቻልም የሚሉ አንዳንድ ታዛቢዎች ለሁሉም የወያኔ ግፈኛ ባለስልጣናትም ሆነ አጋጣሚውን በመጠቀም ሕዝብ የሚበድሉና የሕዝብ ሃብት የሚዘርፉ ሁሉ የኦሞት አባንግ የሰሞኑ አጋጣሚ ጥሩ መማሪያ ነው። ይዘገያል እንጅ ሁሉም ለፍርድ መቅረባቸው ኤኢቀርም ይላሉ።

ዛሬ በዓለማቀፍ ደረጃ በመታደን ላይ የሚገኘው ኦሞት ኦባንግ በጋምቤላ ክልል በተከሰተው አይን ያወጣ የሕዝብ ሃብት ዘረፋና የተደራጀ ሙስና እንደሁም ከ400 በላይ ንጹሃን አኙዋኮችን በግፍ በማስጨፍጨፉ እና በሽዎች ለሚቆጠሩትም ስደት ምክንያት በመሆን ተጠያቂ ነህ በተባለበት ወቅት ሁሉንም ነገር የመራውና ለጭፍቸፋው መሳሪያ ያቀበለኝ የቀድሞው የወያኔው ቁንጮ መለስ ዜናዊ ነው ማለቱ አይዘነጋም።

## በለገጣፎ ለገዳዲ አስደንጋጭ የመሬት ዝርፊያ እየተካሄደ ነው

የኢትዮጵያን ህዝብ ዘርፈዉ ባዱ እጁን ካላስቀሩት እንቅልፍ የማይወስዳቸዉ ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች ከአዲስ አበባ ከተማ በጥቅት ኪሎሜትሮች ርቀት ላይ በምትገኘዉና ለገጣፎ ለገዳዲ ተብላ በምትጠራዉ ከተማ ዉስጥ ከፍተኛ የመሬት ዝርፊያ እያካሄዱ መሆናቸዉን ኦሮሚያ ዉስጥ የሚገኙት የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች ገለጹ። ዘጋቢዎቻችን የከተማዋን ነዋሪዎች አናገረዉ በሰበሰቡት መረጃ መሰረት ለገጠፎ ዉስጥ የአርሶ አደሩ መሬት ከዚህ ቀደም ከተማዋ ዉስጥ ኖረዉም ታይተዉም በማያዉቁ ሰዎች መያዙን ለማወቅ ተችሏል። በቃኝን የማያዉቁ የወያኔ መሪዎች በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙትን የኦሮሞ ተወላጆች ከይዞታቸዉ እያፈናቀሉ መሬታቸዉን መሸጥ በመጀመራቸዉ ከአህዴድ መሪዎች ጋር መጋጨታቸዉ የሚታወስ ሰሆን ይህ ግጭት በተለይ ከመለስ ዜናዊ ሞት በኋላ እየተባባሰ መምጣቱ የሚታወስ ነዉ።

በቅርቡ ኢሳት ቴሌቪዥን ለገጠፎ ከተማ ዉስጥ ያለዉን የመሬት ባለቤትናት የሚያሳይ ሰነድ እጁ ዉስጥ የገባ ሲሆን ከ4 ሺ በላይ ሰዎችን ስም ዝርዝር በያዘው በዚህ ሰነድ ማንነታቸው የማይታወቁ ሰዎች የአባታቸውን ስም ብቻ በመቀያየር ከ 140 እስከ 500 ካሬ ሜትር ቦታዎችን ይዘዋል። አለማየሁ ፣ አልማዝ፣ አለምጸሃይ፣ አሰፋ፣ አበራ ፣ አብርሃም ፣ አበበ የሚሉ ስሞች ከ15 እስከ 30 የሚጠጉ የቦታ ካርታዎችን በስማቸው አሰርተው ይዘዋል። ግለሰቦቹ ቦታውን ያገኙት ከ2000 እስከ 2001 ዓም ባለው የአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ነው። የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ በአንድ ወቅት 15 ሺ በላይ ሰዎች በህገወጥ መንገድ የቦታ ካርታዎችን መያዛቸውን የሚገልጽ መግለጫ ማውጣቱ ይታወቃል። ለኢሳት በደረሰው ሰነድ ላይ ለማየት እንደሚቻለው አብዛኞቹ ሰዎች ቦታዎችን የሚወስዱት ጂ+2 እየተባለ የሚጠራውን ቤት ለመስራት ነው። በከተማው የሚታየውን የቦታ ዘረፋ በተመለከተ የከተማው ነዋሪ ህዝብ በተደጋጋሚ የተቃውሞ ሰልፍ አድርጓል። የኦሮሚያ ክልል ችግሩን ለመፍታት ቃል ቢገባም የከተማዋ አመራሮች ወርደው በሌሎች እንዲተኩ ከማድረግና የተተኩትም ሰዎች ተመሳሳይ ድርጊት ከመፈጸምው የተለወጠ ነገር አለመኖሩን ነዋሪዎች ይናገራሉ።

በለገጣፎ ለገዳዲ በኮምኒኬሽን ሰራተኛነት ሲያገለግል የነበረው የገዢው ፓርቲ አባል ወጣት መኮንን ተስፋየ በከተማዋ ውስጥ የሚፈጸመውን ዝርፊያ ከሌሎች ወጣቶች ጋር በመሆን በማጋለጥ በኩል ከፍተኛ ሚና ሲጫወት ከቆየ በሁዋላ፣ በመጨረሻም ህይወቱን ለማትረፍ ሲል በቅርቡ ከአገር ተሰዷል። ወጣት መኮንን እንደሚለው እብዛኞቹ የከተማዋ ቦታዎች በባለስልጣናት የተቸበቸቡ ናቸው። በሙስና የተከሰሱት የቀድሞው የገቢዎችና ጉምሩክ ምክትል ሃላፊ አቶ ገብረውሃድ ወልደ ጊዮርጊስ በዚሁ በለገጣፎ ለገዳዲ የቦታ ካርታ በብዛት ይዘው ከተገኙት መካከል ናቸው።

## አገር ዉስጥና በውጭ አገሮች የሚኖሩ የአማራ ተወላጆች

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ሰብስቦ ማስተጋባቱ ያስቆጣቸው በርካታ አስተያየታቸውን ያደረሱን ወገኖች ይህ ሁሉ የአማራን ህዝብ ሞራል ለመምታትና ቅስም ለመስበር እየተደረገ ላለው የፋሽስቱ ወያኔ አላማ ማስፈፀሚያ አንዱ አካል መሆኑን ገልፀዋል። የአማራው ህዝብ ሰንፋጭ የሆነ ትምክህተኝነት የተጠናወተው ነው። ይህም ለስደት ዳርጎታል። የአማራው ህዝብ የትምክህት ልጋጉን ማራገፍ አለበት፡ አማራው በባዶ እግሩ እየሄደ የሚናገረው ነገር ግን መርዝ ነው ሲሉ ለክልሉ ህዝብ ያለውን ከፍተኛ ንቀትና ጥላቻ በስድብ አጅቦ ማስተላለፉ የሚታወስ ነው። በጉዳዩ ዙሪያ በርካታ የተቃውሞ ሰልፎች በሃገር ውስጥና በውጭ እንደሚደረጉ፡ ይህ ቅጥረኛ የፋሽስት አገልጋይ ከሃላፊነቱ እንዲወርድና ለፍርድ እንዲቀርብ ለማድረግ እንቅስቃሴዎች በስፋት መጀምራቸውን ለማወቅ ተችሏል እንደ ምንጮቻችን ዘገባ።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ወያኔ በእድገት ስም ክልሎችን በራሱ ቁጥጥር ስር ለማስገባት ዳር ዳር ማለቱ ተሰማ

በፌደራሊዝም ስም የኢትዮጵያን ህዝብ ከሃያ አመታት በላይ ጨምድዶ የገዛዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ እስከዛሬ ርግጦ የገዛዉ አልበቃ ብሎት አንዳንድ ክልሎችን በሞግዚትነት ለማስተዳደር ሽር ጉድ መጀመሩን ዉስጥ አዋቂ ምንጮች ከአዲስ አበባ በላኩልን ዜና ገለጹ። ወያኔ ወደ አዲስ አበባ ሲገዝ እንደ መጋገሪ የተጠቀመበትን ኢህአዴግን አሁንም እንደ መሳሪያ በመጠቀም ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ሃረሪ፣ ድሬዳዋ፣ ሶማሊና አፋር ክልሎችን አስተዳድራለሁ በሚል ሰበብ እርግጫዉንና ዘረኝነቱን ለማስፋፋት ቆርጦ የተነሳ ይመስላል። እንደ ዉስጥ አዋቂ ምንጮቻችን አባባል ወያኔና የወያኔ አሽከር የሆኑት ብአዴን፣ ኦህዴድና ደኢህዴን ከላይ የተጠቀሱትን ክልሎች ለማስተዳደርና በበላይነት ለመምራት ተከፋፍለዉ ስራቸዉን ለመጀመር በዝግጅት ላይ ናቸዉ።

በኢትዮጵያ ህገ መንግስት አንቀጽ 52 ክልሎች ራስን በራስ የማስተዳደር ስልጣን የተሰጣቸው ሲሆን፣ ስልጣናቸውን ተጠቅመመውም የክልሉን የኢኮኖሚ፣ የመሀበራዊና የልማት ፖሊሲ ስትራቴጂና እቅድ የማውጣት ስልጣን ተሰጥቷቸዋል። ይሁን እንጅ የፌደራሉ መንግስት እራሱ በሚወክላቸው አስፈጻሚዎችን አዳጊ የተባሉትን ክልሎች በተዘዋዋሪ መንገድ ሲያስተዳደር ቢቆይም፣ አሁን ግን ግንባሩ አዳጊ ክልሎችን በመከፋፈል ለማስተዳደር ውሳኔ ላይ መድረሱን የውስጥ ምንጮች ገልጸዋል።በዚህ አዲስ የስልጣን ድልድል መሰረት አዳጊ ክልሎች ያለ አውራ ፓርቲዎች እውቅና ምንም አይነት ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን አያደርጉም።

አፋር ክልልን የሚያስተዳድረው አፍዴፓ በህወሃት ስር ሆኖ የአፋር ክልልን የሚያስተዳድር ሲሆን፣ በክልሉ ምክር ቤት ስብሰባ ወቅትም የትግራይ ክልል ፕሬዚዳንትና ምክትላቸው ይገኛሉ። በትግራይ ክልል የምክር ቤት ስብሰባ ወቅት ግን የአፋር ክልል ፕሬዚዳንት እና ምክትላቸው አይገኙም። ኦሮምያን የሚያስተዳድረው ኦህዴድ በበኩሉ በህወሃት ደጋፊነት የሶማሊ ክልልን የማስተዳደር ሃላፊነት ሲሰጠው ፣ ሶማሊ ክልል በበኩሉ በኦህዴድ እየታዘዘ ድሬዳዋን ያስተዳድራል።የአማራውን ክልል የሚመራው ብአዴን በበኩሉ በአቶ ደመቀ መኮንን በሚሰጥ ውሳኔ የቤንሻንጉል ጉሙዝን እንደሚያስተዳድር ታውቋል። የቤንሻንጉል ጉሙዝ ፖለቲካዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ ግንኙነቱ ከብአዴን ጋር ይሆናል።

ኢህአዴግ የወሰደው ፖለቲካዊ እርምጃ በአዳጊ ክልሎች ውስጥ የሚፈጥረው የተለየ ስሜት እንደማይኖር የውስጥ ምንጮች ይገልጻሉ። ቀደም ብሎ አዳጊ ክልሎች በፌደራል ባለስልጣናት ጣልቃ ገብነት ይተዳደሩ እንደነበር የሚጠቅሱት እነዚሁ ምንጮች፣ አሁን ዋናዎቹ ክልሎች አዳጊ ክልሎችን በመከፋፈል ለማስተዳደር በመወሰናቸው አዳጊ ክልሎች የሚያሰሙት ተቃውሞ አይኖርም ብለዋል የአዲስ አበባ መስተዳድር እነዚህን ከተሞች ከአዲስ አበባ ጋር ለመቀላቀል ቢያቅድም፣ የኦሮምያ ክልል ፈቃደኛ ባለመሆኑ እስካሁን አልተሰካም። የኦሮምያ ክልል ከእንግዲህ ለአዲስ አበባ የምንሰጠው መሬት የለም በሚል አቋሙ በመጽናቱ የፌደራሉ መንግስት የቤቶች ልማት እቅድን ለመተግበር እየተሳነው መጥቷል። ከወጣት መኮንን ተስፋየ ጋር ያደረግነውን ቃለምልልስ በቅርቡ ይቀርባል።

## የመሬት ቅርምቱ እንደገና ሲቃኝ

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

ግንቦት 7 የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚካሄደዉን የመሬት ቅርምት አጥብቆ የተቃወመዉ ገና ከጥዋቱ ነዉ። ግንቦት ሰባት ኢትዮጵያ ዉስጥ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፤ የገበሬዉን ህይወት ለመለወጥና የግብርናዉን ዘርፍ ምርታማነት ለማሳደግ መፍትሄዉ ለገበሬዉ የብድር፤ የማዳበሪያና የቴክኖሎጂ አገልግሎት መስጠትና ገበሬዉን የመሬት ባለቤት ማድረግ እንጂ የአገር ቤቱን ገበሬ ከመሬቱ እያፈናቀሉ መሬቱን ለዉጭ ባለኃብቶች መሸጥ አይደለም የሚል የጸና እምነት አለዉ።

የህወሀት መሪዎች እጃችንን አጣምረን ካየናቸዉና ጀርባችንን ሰጥተን ካዳመጣናቸዉ የማይነግሩንና የማያደርጉት ነገር እንደሌለ አግራቸዉ አዲስ አበባን ከረገጠበት ግዜ ጀምሮ አንድ፤ ሁለት ሦስት እያሉ ተራ በተራ አሳይተዉናል፤ እኛም እያንዳንዷን የወያኔ ጉድ በሰማን ቁጥር ከጩኸት አልፈን የፈይድነዉ ምንም ፋይዳ ስለሌለ ወያኔ በጥፋት ላይ ጥፋት በበደል ላይ በደል እየፈጸመብን ኖሯል። ግንቦት ሰባት የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ዛሬ ወቅቱ እኛ ወያኔን የምንሰማበት ሳይሆን ወያኔ እኛን የሚሰማበት አለዚያም የተባበረ ክንዳችንን ጥንካሬ መቅመስ ያለበት ወቅት ነዉ ብሎ ያምናል። ዛሬ ወያኔ ድንበር ቆረሶ ሸጠ፤ ለምለም መሬታችንን ለባዕዳን በርካሽ ቸበቸበ፤አማራዉን አፈናቀለ እያልን የተብታተነ አጀንዳ እየያዝን በየፊናችን ወያኔን በተናጠል የምንገጥምበት ግዜ አይደለም። የኢትዮጵያ ችግሮች እጅግ በጣም ብዙዎች ናቸዉ፤ የችግሮቻችን ባለቤት ግን አንድ ወያኔ ነዉ። ስለዚህ ክንዶቻችንን አገጣጥመንና ትከሻ ለትከሻ ተደጋግፈን ይህንን የአገራችንን ቁጥር አንድ ጠላት እናስወግድ እያለ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዉ የትግል ጥሪ ያስተላልፋል።

## አሸንፈው በአንድነትህ

ከልቦናህ ወሬ ለመቅዳት፤
ከአፍህ ነገር ለመስለብ
ወያኔ በነካካህ በቆሰቆሰህ ቁጥር፤
ተጠራርተህ በመሰባሰብ
ቁጣህን በአደባባይ ዘርግፈህ
ይውረድ በቃ! ብለህ ጮኸህ

አንድ መስለህ
አብረህ ቆመህ
በማግስቱ ተለያይተህ
ቡድን ፈጥረህ ተበጣጥሰህ
ተሰዳድበህ ተኮራርፈህ
ባንተው ዱላ አንተን መተህ
እንደገና ደግሞ በዓመት
ተገናኝተህ ጮኸህበት
ብትመለስ ሰዳድበኸው
ምን ሊጠቅምህ? ምን ልትጎዳው?
ምኞት ህልምህ ነፃነትህ
እየራቀ የድል ቀንህ
ይጨምራል ግፍ በደልህ
አሸንፈው በአንድነትህ

አለዛ ግን ጥንካሬውን እየለካ፤
ባንተ ሰቀቀን
እየዶለተብህ ሌት ተቀን
እየከፋፈለ በታትኖህ
አራርቆ አለያይቶህ
የሀገር ፍቅርህን አልቦ
ወኔህን ከልብህ ሰልቦ
ድምጥማጥህን ሳያጠፋ
ሳያጨልም ያንተን ተስፋ
እመነኝ እንደማያንቀላፋ።

አይግረምህ ይሄን ቢያደርግ
የጭካኔ ስራ'ኮ ነው የሱማ ወግ
እንደወባ ህመምተኛ፣ መጥፎ ቅዠት
መጨበጫ አሳጥቶህ፣ ባጉል ውሸት
የዘረኛ መለያውን ያንገት ክታብ
እላዩ ላይ አንጠልጥሎ በማዋከብ
በስቃይህ በርሃብህ በሞትህ ላይ
አይደል እንዴ? የሚአፈራው የሱን ሲሳይ

ከወጣማ ከበደል ሕግ
ካሳደረህ በወግ ማዕረግ
ኑሮህን ሳያዋከብ
አፍህን ሳይሸብብ
ነፍስህን ሳያሳቅቅ
አቅምህን ሳያደቅ
ዝም ብሎህ ከነጋበት
ሳያቆስልህ ከመሸበት
አንድ ሆነህ ተሰባስበህ
ጊዜ አግኝተህ ተመካከረህ
ታጠፋው የል ምን ያድርግህ
ደግሞስ እንደው ያ እንኳን ባይሆን
እንዴት ይስጥህ ሠላምህን?
ከየት ያምጣው አላመሉ
አለ ውልዱ አለ ትከሉ
ኢትዮጵያዊ ቅድመ ነፍሱ
ብሔራዊ እስትንፋሱ
በዘር ደዌ ተመርዞ
ውስጡ ሞቶ ተገንዞ
ሀገር ውደድ የምትለው
ያንን ፍቅር ከየት ያምጣው?
ለእኩልነት ምታንጋጥጥ
ነፃነትን ምትቀላውጥ
የት ኖሮት ነው ላንተ የሚሰጥ?

ምክር ልስጥህ ስማኝ ይልቅ
ሳትለያይ ሳትራራቅ
ሳትባባል ትንሽ ትልቅ
ከየቦታው ተሰባስበህ
ተመካከረህ ከስር ነቅለህ

ስቃይህን ስትግተው
ርሀብህን ስትጋብዘው
የሚሸሸው የፈራው ሞት
እላዩ ላይ ሲሰፍርበት
ያን ጊዜ ነው የሚአልቅለት

አለዛ ግን አንዳንድ ቀን ተሰባስበህ
ይውረድ በቃ! ብለህ ጮኸህ
ሰው ሲታሰር ፎቶ አውጥተህ
ሲሞትብህ ሻማ አብርተህ
አንድ መስለህ
አብረህ ቆመህ
በማግስቱ ተለያይተህ
ቡድን ፈጥረህ ተበጣጥሰህ
ተሰዳድበህ ተኮራርፈህ
ባንተው ዱላ አንተን መተህ
እንደገና ደግሞ በዓመት
ተገናኝተህ ጮኸህበት
ብትመለስ ሰዳድበኸው
ምን ሊጠቅምህ? ምን ልትጎዳው
ምኞት ህልምህ ነፃነትህ
እየራቀ የድል ቀንህ
ይጨምራል ግፍ በደልህ
አሸንፈው በአንድነትህ

*ወለላዬ ከስዊድን*
*welelaye2@yahoo.com*